## ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹ የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር “፵፱/፳፻፰” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪ ማሻሻያ

የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፮/፪ሺ፰ እንደሚከተለው ተሻሽሎአል፡፡

፩ የአዋጁ አንቀፅ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፱) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፱) ተተክቷል፡፡

“፱,የከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፤

፪ የአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ‹‹ሐ››ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ፊደል ‹‹ሐ›› ተተክቷል፡፡

‹‹ሐ.የከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፤

፫ የአዋጁ አንቀጽ ፮. ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ተተክቶአል፡፡

“፲፪, የወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን

፬ የአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል “ሐ” ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ፊደል “ሐ” ተተክቶአል

“ሐ” የወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን፣

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as the “The Definition of the Powers and Duties and Re-establishment of the Executive and Municipal Service Organs of the Dire Dawa Administration (Amendment) Proclamation No 49 /2016.

## 2. Amendment

The Definition of the Powers and Duties of the Executive and Municipal Service Organs of the Dire Dawa Administration Proclamation No,46/2016 is hereby amended as follows:

1. Sub–Article (9) of Article 6 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new sub article (9);

“9, Urban job Creation and Food security Agency

2. Paragraph (c) of Sub–article (2) of Article 7 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new paragraph (c).

“c, Urban job Creation and Food Security Agency

3. Sub- article (12) of Article 6 of the proclamation is repealed and replaced by the following new sub- article (12)

“12, the youth and sports commission;

4. paragraph (c) of sub-article (1) of Article 7 of the proclamation is repealed and replaced by the following new paragraph (c).

“c, the youth and sports commission

፭ ከአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፱) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳)፣ (፳፩) እና (፳፪) ተጨምረዋል፡፡

"፳.ለህዝብ ጥቅም ሲባል የከተማና የገጠር መሬት ይዞታ እንዲለቀቅ ሲደረግ ለባለ ይዞታው ካሣ ክፍያ ተመኑ ተወስኖ ሲደርሰው ክፍያው እንዲፈፀም ያደርጋል፤

"፳፩.ለህዝብጥቅም ሲባል ከይዞታቸው ላይ የሚነሱ ሰዎችን ወደ ተፈለገው ቦታ ያጓጉዛል፣ መልሰው እንዲቋቋሙ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

"፳፪.ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቁ ቦታዎች ላይ ለሚገኙ በህጉ መሰረት ተነሺ ለሆኑ ሰዎች መንግስት ስለሚካሄደው የልማት ፕሮግራም ግንዛቤ እዲያገኙ ያደርጋል፤

፮. የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፳) ንዑስ አንቀጽ ፳፫ ሆኖአል፡፡

፯. የአዋጁ አንቀጽ ፲፯.ተሸሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ (፲፯) ተተክቶአል፡፡

"፲፯, <u>**የወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን ሥልጠንና ተግባር**</u>

ኮሚሽኑ የሚኩተሉትን ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፰ የአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ተሸሮ በሚኩተለው አዲስ አንቀጽ ፳፪ ተተክቷል፡፡

"፳፪.<u>የከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባር፣</u>

ኤጀንሲው የሚኩተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

5. The following new sub- article (20)፣ (21) and (22) are added under sub – article (19) of Article 12 of the proclamation

"20 Shall coordinate payment of compensation conditions when urban and rural land are expropriated for public good, effect payment when received the amount of compensation payment;

"21.Provide necessary support such as transport and rehabilitation works for displaced possessors for the purpose of public good;

"22,Conduct sensitization program for legally displaced possessor about the on going developmental programs conducted by the government;

6. sub- article (20) of Article 12 of the proclamation is re-numbered as sub- article (23).

7. Article 17 of the proclamation is replaced and replaced by the following new article 17

'17, <u>powers and duties of youth and sport commission</u>

The commission shall have the following powers and duties;

8. Article 22 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new article 22.

''22 <u>Powers and Duties of Urban job Creation and Food Security agency:</u>

The Agency shall have the Powers and Duties to;

፩. የከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ የአስተዳደሩን የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪. የከተሞች የስራ ዕደል ፈጠራና የምግብ ዋስትናን በሚመለከት የፖሊሲ ጥናቶችን ፣ እና ስትራቴጂክ ፕላኖችን እያጠና ያቀርባል፣ ለከተማው ህበረተሰብ የምግብ ዋስትና መረጋገጥ፣ የኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ለመለየት ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫. በፌደራል ደረጃ የከተሞችን የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ስራዎችን ለማስፋትና ለማልማት የወጡትን ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ በከተማው አስተዳደር ውስጥ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲስፋፉና እንዲለሙ እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ልማት መሰረት እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፬.ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋትና ድጋፎችን ለመስጠት እንዲሁም የከተማ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችል ደንቦችን፣ መመሪያዎችና እስታዳርዶችን ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል ፤

፭. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እና የከተማ ምግብ ዋስትና ስትራቴጅዎች በተገቢው ሁኔታ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣ በስትራቴጂዎቹ አፈፃፀም ለሚከሰቱ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፤

1. Prepare the administration development plan in accordance with the urban employment creation and food security strategy, implement up on approval;

2. Study and submit policy idea and strategic plans pertinent to urban employment creation and food security ,facilitate studies on the identification of barriers to ensure food security, enterprises development and competitiveness pertinent to the urban community , implement up on approval;

3. In accordance with the federal policies and strategies promulgated on the promotion and development of urban employment creation and food security , cause the expansion and development of the Micro and Small Enterprises in the urban area thereby serves the purpose of industrial development;

4. Prepare regulation, directive and standards, which enable for the expansion and rendering supporting service to the micro and small scale enterprises as well as enable to ensure food security initiatives ,follow-up its implementation up on approval

5. Ensure the proper implementation of micro and small enterprise development and urban food security strategies, carryout timely response for the problem arises during the implementation of the strategies

፮. በከተማ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በመቅረፅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፯. የከተማ ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አኳያ ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የገንዘብና የማቴርያል ድጋፍ እንዲገኝ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፰. በከተማው የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የሰራ ዕድል ለመፍጠር የስራ አጦች፣መስራት የሚችሉና የማይችሉ ዜጎችን መረጃ በጥናት በመለየት ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤

፱. በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶችን በብዛት በማሳተፍ አምራች ዜጋ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ያደርጋል ፣ ተግባራዊነታቸውንና ውጤት ማስገኘታቸውን ያረጋግጣል፤

፲ የዘርፉ ምርቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ገበያ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ምርቱን ለማስተዋወቅና ህብረተሰቡ ስለ ተቋማቱ ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲኖረው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ትምህርታዊ መግለጫዎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፲፩.በከተማው ህብረተሰብ ውስጥ የሚታየውን የተዛባ የስራ አመለካከት መቀየር የሚያስችሉ ግንዛቤ ማዳበሪያና የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን ያከናውናል፤

6. Design and implement productive urban safety net program;

7. Establish linkage with governmental and civil society organization and facilitate the attainment of financial and material supports so as to ensure the urban food security initiative;

8. Collect information about productive and non productive labor based on a survey and analyze, coordinate and disseminate the same to ensure food security and create employment opportunity in urban areas;

9. Cause the study of micro and small scale business enterprise projects in the city that enables the popular participation of unemployed urban youth and women to be productive citizen , follow up the implementation and the same results;

10. Facilitate the situation for the product of the sector to get domestic and export market access ; in co-operation with concerned organ design different strategies which enable to promote the product and to publicize the institutions among to the residence ;cause the preparation of educational descriptions, coordinate the execution , and follow-up the same;

11. Carryout awareness creation and public mobilization to reverse the distorted attitude of employment behavior among the urban residents;

፲፪ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለማደራጀት፣ ለማጠናከር እና አገልግሎቱን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችል የተሻሻሉ አዳዲስ ሥርዓቶችን በመዘርጋት የማዕከሉን አቋም ይገነባል ፣ ማዕከላቱን ያስተባብራል፤

፲፫ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚውል መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል ፤የድጋፎች ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት ያካሂዳል፤

፲፬ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ያደራጃል፤ይመራል፤ያስተባብራል፤

፲፭ የስልጠና እና የብድር አገልግሎት ቴክኖሎጂና የማምረቻ መሳሪያዎች አቅርቦት ያመቻቻል፣ የገበያ ትስስርና ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፮ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻ፣ የመሸጫ ቦታ ገንብቶ ያቀርባል፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እንዲያገኙ ያስተባብራል፤

፲፯ ሞዴል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ይፈጥራል፣ ያሸጋግራል፤

፲፰ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኦዲትና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፱ በከተማ የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማጥናትና በመቀመር የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ያስፋፋል፤

፳.ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

12. Establish improved system to organize, strengthen as well as for proper service rendering of one stop services, build the capacity of the center , coordinate the centers;

13. Collect , organize information required for development of micro and small scale business enterprises, distribute to the users ; conduct study on the need of supports and supply requirements;

14. Organize, lead coordinate micro and small enterprises ;

15. Facilitate training, credit service, technology and production equipment supplies; and provide supports for marketing linkages;

16. Carryout the construction and provision of production and sales centers, and coordinate the facilitation of industrial extension services the same;

17. Establish model micro and small enterprises, promote the same;

18. Render auditing and inspection service for the micro and small scale enterprises;

19. Study, synthesized and scale up the best practice achieved on urban employment creation and food security interventions ;

20. performed relevant activities necessary for the fulfillment of its objectives

፱. ከአዋጁ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ (፳፱) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳፱) ተጨምሮአል፡፡

"፳፱. ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን መረጃ በጥናት በመለየት ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል ያሰራጫል፤

፲. የአዋጅ አንቀጽ ፵፩ ንስ አንቀጽ (፳፱) ንዑስ አንቀጽ (፴) ሆኖአል፤

፲፩.የአዋጁ አንቀጽ ፵፫ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተተክቶአል፡፡

"፭,በልማት ምክንያት ለሚነሱ ህጋዊ ባለይዞታዎች ምትክ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ ይሰጣል፤

፲፪. የአዋጁ አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቶአል፡፡

"፩,የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን እንዲሁም የአካባቢ ልማት ዝርዝር ፕላኖችን መሠረት በማድረግ የመሬት ልማት እና የከተማ ማደስ የመሬት ፍላጎት ጥናት ሥራ ያከናውናል

፲፫. የአዋጁ አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተተክቶአል፡፡

9. The following new sub-article (29) is added under sub- article (28) of the proclamation.

''29. Collect information on social marginalized citizens based on a survey and analyze, coordinate ,disseminate the same

10. Sub.article (29) of artile 41 of the proclamation is re-numbered as sub-article (30);

11. Sub- article (5) of article 43 of the proclamation is repealed and by the following new sub- article (5)

"(5),provide replacement for residential housing construction land for displaced legal owners;

12. Sub- article (1) of Article 47 of the proclamation is repealed and replaced by the following new sub-article (1).

"1, conduct study works on land development and city renewal based on the structural plan as well as specific local development

13. Sub- article (5) of Article (47) of the proclamation is repealed and replaced by the following new sub-article (5):-

"፭,በልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችና በመልሶ ማልማት ምክንያት ተነሺ ለሚሆኑ ሰዎች በህግ መሠረት ምትክ ቦታና የምትክ ቤት መቀበያ ሰርተፍኬት ይሰጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

## ፫.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ድሬዳዋ ጥር ፳፩ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም**

**ኢብራሂም ዑስማን**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**

"5, issue certificate of substitute plot and house receiving certificate to persons displaced due to different development and renewal works in the city and follow up the execution thereof;

## 3. <u>Effective Date</u>

This proclamation shall come in to force up on the date of publication in the Dire Negarit Gazeta;

**Done at Dire Dawa, this 31st Day of <u>January</u>,2016**

**IBRAHIM USMAN MAYOR OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION**